ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭ ፣ መጋቢት ፳፻፲፭ ዓ.ም

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



በዓለማቀፍ ደረጃ የፕላስቲክ ብክለትን ለመግታት ያለመና እ.አ.አ. በ 2024 ወደ ተግባር የሚገባ አስገዳጅ ታሪካዊ ረቂቅ ህግ ተቀባይነት አገኘ

በዚህ እትም. . .

ዘላቂነት ያላቸው የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች ተደራሽነት በኢትዮጵያ ፪

ዜናዎች ፪

ሁነቶች ፫

ስቶክሆልም +50 – ለሀገራዊው የምክክር መድረክ ቅድመ-ዝግጅት ፫

ልዩ ልዩ ሀትመቶች ፫



ዋና አዘጋጅ፥ ንጉሱ ለማ ገብሬ

አዘጋጆች፥ ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

አምደኞች፥ መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

ግራፊክስና ሌይአውት፥ አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭

ዜናዎች

የፕላስቲክ ብክለትን መግታት፤ ዓለምአቀፍዊ አስገዳጅ የህግ ስርዐትን መዘርጋት

የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) በየዓመቱ የሚያካሂደው የአካባቢ ጉባኤ አምስተኛው ዙር ስብሰባ በዘንድሮ አመት በኬንያ ናይሮቢ ተካሂዷል። የጉባኤው የመጀመርያው ዙር የበየነ መረብ ክፍለ ጊዜ እ.አ.አ ከየካቲት 22-26 ቀን 2021 የተካሄደ ሲሆን ሁለተኛው ዙር ደግሞ በበይነ መረብ እና በአካል እ.አ.አ ከጥር 28 - የካቲት 2 ቀን 2022 ተካሂዷል።

የዘንድሮው ጉባኤ ካሳለፋቸው ልዩ ውሳኔዎች አንዱ በከፍተኛ ብዛት እና ፍጥነት እየጨመረ የመጣውን የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ብክለትን ለመግታት የሚያስችል ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ ማዘጋጀት ነው። በረቂቁ ህግ መሰረት የፕላስቲክ ብክለት በዘላቂ ልማት፣ በአካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያሳደረ ነው። በመሆኑም የዚህ ህግ መጽደቅ የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ እ.ኤ.አ. በመስከረም 25 ቀን 2015 ያፀደቀውንና እስከ 2030 የሚተገበረውን የዘላቂ ልማት ግቦች አጀንዳ ስኬት እንዲሁም ድርጅቱ እ.አ.አ. በ1992 የአካባቢ እና ልማት መርሆዎችን ያፀደቀበትን የውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 70/1 እንደገና እንደሚያረጋግጥ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። ምንጭ

ሴቶችን ማብቃት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች አይበገሬነትን ለመገንባትና በድንገተኛ አደጋዎች ጊዜ ችግሮችን የመቋቋም አቅምን ለማጎልበት ወሳኝ ነው

የ2022 ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን "የዛሬ የስርዓተ ጾታ እኩልነት ዘላቂነት ላለው ነገ!" በሚል መሪ ሀሳብ ተከብሯል። የዘንድሮው ጭብጥ በዋናነት ያተኮረው በአየር ንብረት ለውጥ ቀውስ እና በአደጋ ስጋት ቅነሳ ላይ የፆታ እኩልነትን ማሳደግ ላይ ነው።

እንደ የተባበሩት መንግስታት የስነ-ህዝብ ፈንድ (UNFPA) ጋዜጣዊ መግለጫ "ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን መጋቢት 8 ቀን ሲከበር፣ በዓለም ላይ ያሉ በርካታ ሴቶች፣ ህፃናት እና ሌሎች ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ኮቪድ-19 ከደቀነባቸው ፈተናዎች በተጨማሪ በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥ ወድቀዋል።

የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከግሎባል ግሪን ግሮውዝ ኢንስቲትዩት (GGGI) እና ሳውዝ ሳውዝ ኖርዝ (SSN) ተቋም ጋር በመተባበር "እኔም የእህቴ ጠባቂ ነኝ" በሚል መሪ ቃል አለም አቀፍ የሴቶች ቀንን እ.አ.አ መጋቢት 21 ቀን 2022 በአዳማ ከተማ አክብሯል። በበዓሉ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ጌታሁን ጋረደው እንዳሉት "ሴቶችን ከማብቃት ጋር በተያያዘ ለውጥ እንዲመጣ ከተፈለገ ይህን ቀን በየዓመቱ እየተገናኙ ከማክበር ባለፈ ሴቶችን ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራዊ እርምጃዎች ላይ ማተኮር አለብን!" ብለዋል።

ዘላቂነት ያላቸው የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች ተደራሽነት በኢትዮጵያ

- ግርማ ገመቹ፣ በኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ህጎች ተከባሪነት ዳይሬክተር ጀነራል

ኢትዮጵያ ለአካባቢ ጥበቃ ተስማሚ የሆኑ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማስፋፋት የአፍሪካ አረንጓዴ የማምረቻ ተቋማት ማዕከል የመሆን አላማን አስቀምጣ በመስራት ላይ ትገኛለች። በቅርቡ ተግባራዊ የሆነው የሞጆ-ጅቡቲ-አውሮፓ ሎጅስቲክስ ኮሪደር፣ የአየር ንብረት ለውጥን አሉታዊ ተፅኖዎች የመቋቋም አቅምን በማጎልበት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከተወሰዱ ቁልፍ የመንግስት ውጥኖች መካከል አንዱ ነው። ይሁንና በሀገራችን የማቀዝቀዣ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ዝቅተኛ ሲሆን ማቀዝቀዣዎችን በዘላቂነት የመጠቀም ሀገራዊ ልማድም ደካማ ነው። ይህም በመሆኑ የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ከልማት አጋሮች ጋር በመተባበር የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቀነስ ተስማሚና ሃይል ቆጣቢ የሆኑ የማቀዝቀዣ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ስራ ለማስገባት የሚረዳ ጥናት ለማከናወን የሚረዳ የቴክኒካዊና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት ግምገማ በተመረጡት ዘርፎች ማለትም በግብርና፣ በንግድ፣ በትራንስፖርት እና በጤና ዘርፎች በማከናወን ላይ ይገኛል። "ዘላቂነት ያላቸውን የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች ተደራሽነት በኢትዮጵያ ማቋቋም" በሚል ርዕስ የሚተገበረው ፕሮጀክት ከተሻለ ተደራሽነት የሚገኙ ጥቅሞችን ማስረጃዎች፣ እንዲሁም የሚያስከትለውን የአየር ንብረት እና የዘላቂ ልማት ጥቅሞች ለማስላት የሚያስፈልጉ ዘዴዎችን ያዘጋጃል።

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት አካል የሆኑት የፓሪስ ስምምነት እንዲሁም የኦዞን ንጣፎችን የሚጎዱ ንጥረ ነገሮችን ለመከላከል የተደረሰው የሞንትሪያል ፕሮቶኮልና የኪጋሊ ማሻሻያ ስምምነት አባል ሀገር ነች። የሞንትሪያል ፕሮቶኮል የኪጋሊ ማሻሻያ፣ የሃይድሮ ፍሎሮካርቦን (HFCs) ፍጆታ እና ምርትን ቀስ በቀስ ለመቀነስ በህጋዊ መልኩ አስገዳጅ የሆነ ዓለም አቀፍ ስምምነት ነው። በመሆኑም ሀገሪቱ የማቀዝቀዣ መሳሪያዎችን በሚጠቀሙ ዘርፎች የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዞች

ወደ ገፅ ፫

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭

ከገፅ ፪ የቀጠለ

በመቀነስ እና እንደ ሃይድሮ ፍሎሮካርቦን (HFCs) ባሉ ማቀዝቀዣ መሳሪያዎች ላይ የሚውሉትን ኃይለኛ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ዘላቂነት ባላቸው የአረንጓዴ ቴክኖሎጂ አማራጮች በመተካት ለአረንጓዴ ልማት ቁርጠኛ ነች።

ዘላቂ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶችን ተደራሽነት በኢትዮጵያ ማቋቋም" የሚባለው ፕሮጀክት በኢትዮጵያ የተሻሻለው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ (NDC) ግቦች አፈፃፀም አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ሴክሬተሪያት እ.አ.አ. በጁላይ 2021 የተላከ ሲሆን ይህም ዘላቂነት ያላቸውን ማቀዝቀዣዎች በጠቀም ከዘርፉ የሚለቀቀው የሃይድሮ ፍሎሮካርቦን ጋዝ ልቀት መቀነስ ላይ ተጨማሪ ጥናት እንደሚያካሄድ ይገልጻል።

ፕሮጀክቱ ኢትዮጲያ ወደ ዘላቂ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች አጠቃቀም ለመሸጋገር ባወጣችው እቅድ መሰረት፣ በፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት እና በኪጋሊ ማሻሻያ መካከል ያለውን መስተጋብር ይዳስሳል። እንዲሁም ፕሮጀክቱ የሚያካሂደው ጥናት በተመረጡ ሴክተሮች ላይ የማቀዝቀዣ ቴክኖሎጂዎችን በመተንተን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ይለያል። ይህም ኢትዮጲያ በሞንትሪያል ስምምነት የኪጋሊ ማሻሻያ በገባችው ሃላፊነት መሰረት ለምታቀርበው ሪፖርት ግብዐት ይሆናል። ጥናቱ በተለያዩ ዘርፎች የተለዩ የአየር ንብረት ለውጥ ማስተሠርያ አማራጮችን (Mitigation Options) በመመርመር አማራጮቹ እንዴት ኢትዮጲያ ከኪጋሊ ማሻሻያ ባሻገር የሃይድሮ ፍሎሮካርቦን ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ ለምታደርገው ጥረት አስተዋፅኦ ማድረግ እንደሚችሉ ይመረምራል። ይህ ፕሮጀክት በገንዘብ የሚደገፈው ክሊን ኩሊንግ ኮላቦሬቲቭ በተሰኘ ተቋም ሲሆን ሳውዝ ሳውዝ ኖርዝ እና ፐርስፔክቲቭስ ክላይሜት ግሩፕ በተሰኙ ተቋማት አማካኝነት እየተተገበረ ይገኛል።

የሃይድሮክሎሮፍሎሮካርቦን የግልጋሎት ዘመን ማክተም

ኢትዮጵያ አስገዳጅና ሊተገበሩ የሚገባቸው ዒላማዎችንና ስልቶችን የያዘው የሞንትሪያል ስምምነትን እንደተቀበለ ሀገር ከማቀዝቀዣዎች የሚወጡና የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስ ይቻል ዘንድ ከማቀዝቀዣ መሳሪያዎች የሚወጡና ኦዞንን የሚያሳሱ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ የመገልገያ መሳሪያዎቹን ተጠቃሚነት ቀስ በቀስ መቀነስ ይጠበቅባታል። ለዚሁ ተግባራዊነት ሲባል ኢትዮጵያ የፍሎሮክሎሮሃይድሮካርቦን አመንጪ ቁሶችን በሂደት ከስራ ለማውጣት ታስቦ የተዘጋጀው የአስተዳደር እቅዷን መሰረት በማድረግ በርካታ አበረታች እርምጃዎችን ወስዳለች። የዕቅዱ ዓላማ በኢትዮጵያ የፍሎሮክሎሮካርቦንን የሚያመነጩ ማቀዝቀዣዎችን ፍጆታን በመቀነስና ሀይል ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማስተዋወቅና ተግባራዊ በማድረግ የኦዞን አሳሿዎችን ልቀት መቀነስና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን መከላከል ነው።

የሀይድሮክሎሮፍሎሮካርቦን ቅነሳ ምዕራፍ 1 ስራ የተከናወነው እ.አ.አ. ከ2011-2021 ባለው ጊዜ ሲሆን በዚህ ምዕራፍ 30% ማለትም 3.58 የኦዞን አሳሿ አቅም (ODP) ቶን የሀይድሮክሎሮፍሎሮ ካርቦን ለመቀነስ የታቀደ ሲሆን፤ በ2021 የተመዘገበው የ 47.5% ቅነሳም ከታቀደው በላይ ነው። የሀይድሮክሎሮፍሎሮ ካርቦንን ለመቀነስ የተያዘው እቅድ የሀገሪቱ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ውስጥ የተካተተ ሲሆን መንግስት ለስራው ያለውን ቁርጠኝነት በግልፅ የሚያሳይ ነው። ሁለተኛው ምዕራፍ የሀይድሮክሎሮፍሎሮካርቦን ቅነሳ ዕቅድ በቅርቡ በ653,570 የአሜሪካ ዶላር በጀት የፀደቀ ሲሆን ይህም ሀብት የተገኘው ታዳጊ ሀገራት የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ነገሮችን ለመቀነስ የገቡትን ግዴታ እንዲወጡ ለማገዝ ታስቦ ከተዘጋጀው የገንዘብ ድጋፍ ነው።

ኢትዮጵያ እ.አ.አ. እስከ 2030 ሀይድሮክሎሮፍሎሮካርቦንን ሙሉ በሙሉ የማስወገድ እቅድ ሲኖራት ወደ ሀገር ውስጥም እንዳይገባ የምታግድ ይሆናል። ይሁንና ከ2030 እስከ 2040 ባለው ጊዜ ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ላሉ ቁሳቁሶች ጥገና የሚውል እና ከሞንትሪያል ፕሮቶኮል ድንጋጌዎች ጋር የማይጋጩትን አይመለከትም። ለዚህም ስኬት ሲባል ብሔራዊ ኦዞን ዩኒት (NOU) ከተለያዩ ሴክተሮች ማለትም ከጤና ሚኒስቴር ፣ ከግብርና ሚኒስቴር ፣ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር እና ከኢትዮጵያ አየር መንገድ መረጃዎችን ይሰበስባል። በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ውስጥ የሚገኘው ብሄራዊ የኦዞን ዩኒት የዚህን ስራ ሀገራዊ ኢላማ ለማሳካት አጋር ድርጅቶች በጋራ የሚሰሩበትን የጋራ መድረክ ያዘጋጃል።

የሃይድሮፍሎሮካርቦን አጠቃቀምን መቀነስ

ኢትዮጵያ የኪጋሊ ማሻሻያን እ.ኤ.አ. በ2019 የህጎቿ አካል በማድረግ በ10 አመታት ውስጥ ሃይድሮፍሎሮካርቦንን ለመቀነስ አቅዳለች። ሃይድሮፍሎሮካርቦኖችን ሚያመነጩ ቁሳቁሶች የኦዞን ሽፋን ላይ ጉዳት ስለሌላቸው በሞንትሪያል ፕሮቶኮል የተከለከሉትን ንጥረ ነገሮች ለመተካት ጥቅም ላይ ውለው ነበር።

ወደ ገፅ ፬

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭

ከገፅ ፫ የቀጠለ

ይሁን እንጂ ሃይድሮፍሎሮካርቦኖች ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ኃይለኛ የሙቀት አማቂ ጋዞች ናቸው። ስለዚህም የኪጋሊ ማሻሻያ እነዚህን ጋዞች ለሀገራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ጥረቶች አስተዋፅዖ ለማድረግ ሀገራት ለመቀነስ በሚወስኑት የኬሚካል ንጥረ ነገሮች ዝርዝር ውስጥ አካቷቸዋል። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሀገራዊ አቅምን በመገምገም በካይ ጋዞቹን ለማስወገድ የሚረዱ የሀይድሮፍሎሮካርበን ወቅታዊ አጠቃቀም እና ተመራጭ የሆኑ ጋዞቹን የመቀነሻ እርምጃዎችን መለየት ተግባራት በማከናወን ላይ ይገኛል። ለዚህም ስኬት እ.ኤ.አ. በ 2016 የተጠናው አጠቃላይ የአዞን አሳሺ ንጥረ ነገሮች ዝርዝር በወቅታዊ መረጃዎች በማዳበር ስራ ላይ ይውላል።

የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የተለያዩ የጉምሩክ ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በኪጋሊ ማሻሻያ መሰረት የሃይድሮፍሎሮካርበን አመንጪ ቁሶችን ጠቀሜታን ለመቀነስ ከተመረጡና እየሰሩ ከሚገኙ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላት መካከል ይጠቀሳሉ። በሀገሪቱ 14 የኮሚሽኑ ኬላዎች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 5ቱ ማለትም ጅግጅጋ፣ ሞጆ፣ አዳማ፣ ድሬዳዋ እና ቃሊቲ ዋና ዋናዎቹ ማቀዝቀዣዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበት መንገዶች ናቸው። መንግስት በነዚህ የጉምሩክ ኬላዎች ተዛማጅነት ያላቸውን ምርቶች በድንገት ፈትሸው የሚለዩ መመርመሪያዎች እና ባለሞያዎችን መድቦ በማሠራት ላይ ይገኛል። ይሁንና መጠነ ሰፊ የባለሞያዎች ፍልሰት በዘርፉ የሚስተዋል በመሆኑ ያለመታከት አዳዲስ ባለሞያዎችን ማሰልጠንን ይጠይቃል፤ ይህም ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ ስራውን አዳካች ያደርገዋል።

ሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ አካላት በሀገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት እና ኮሌጆች ናቸው። በአራት ክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ማለትም በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በትግራይና በደቡብ እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ የሚገኙ ተቋማት ተመርጠው በአዞን አሳሺ ንጥረ ነገሮች እና ተያያዥ የቁጥጥር ግዴታዎች ላይ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም ለነዚህ ተቋማት ለስራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች እየቀረበ ነው። ይሁን እንጂ ስልጠናዎችን ወደታች ለማውረድና ለእነዚህ ተቋማት ዘላቂ ድጋፍ ለመስጠት ሰፊ የዜጎች ተሳትፎ ያስፈልጋል።

የዘርፍ ትግበራ

የኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዘላቂ የማቀዝቀዣዎች እንቅስቃሴን ለመጀመር የተለያዩ ዘርፎች በመፈተሽ ላይ ይገኛል። በዚህ አኳያ አንዱና ቅድሚያ የሚሰጠው በርካታ ማቀዝቀዣዎች ያለው ዘርፍ የግብርና ዘርፍ ነው። የጤናው ዘርፍም ተስፋ ያለው ሲሆን በአንፃራዊነት በጥሩ ሁኔታ የተደራጀ እና መረጃን በስርዓት የያዘ ሲሆን በርካታ ማቀዝቀዣዎችን ለተለያዩ ተግባራት ለክትባት ስርጭት፣ ለክትባት መድሀኒቶች ማከማቻ እና ማጓጓዣነትን ጨምሮ ይጠቀማል። በተጨማሪም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ለጤናው ዘርፍ አዞንን የሚያሳሱ ንጥረ ነገሮችን የሚለቁ አሮጌ የማቀዝቀዣ ዕቃዎች አወጋገድ ላይ መመሪያዎችን በማዘጋጀት አግዟል።

የመጠጥ ኢንዱስትሪኦች የራሳቸው በርካታ የማቅዝቀዣ ሰንሰለት ያላቸው በመሆኑ ሌላው አቅም ያለው ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍም የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የማቀዝቀዣ መሳሪያዎቹን የሚጠግኑባቸውን ማዕከሎች በባለስልጣኑ መመሪያ መሰረት በአንድ ማዕከል በማደራጀት እና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ጋዞችን መጠቀም ችለዋል።

በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ላይ የሚገኙት አምስት ጋዝ አስመጪዎች ብቻ ናቸው። ከእንደዚህ ያሉ ጥቂት አስመጪ አካላት ጋር በቅንጅት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን መቆጣጠር ውጤታማ ያየሆናል ተብሎ ይታሰባል።

ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነፃፀር በኢትዮጵያ የማቀዝቀዣ ሰንሰለቶች በብዛት ባይገኙም ዘርፉ ባለፉት አሥርተ ዓመታት ከሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ጋር ትይዩ ዕድገት አስመዝግቧል። ኢትዮጵያ በቀጣይ 10 ዓመታት እንዲተገበር ባዘጋጀችው የልማት እቅድ ላይ በተለይ በግብርና እና ትራንስፖርት ዘርፎች ዘላቂ የሆኑ የማቀዝቀዣዎች አቅርቦትን ለማሳደግ ታቅዷል። ስለሆነም ዘላቂ እና አነስተኛ የአለም የአየር ሙቀት የመጨመር አቅም ያላቸው የተፈጥሮ ማቀዝቀዣዎች ለምሳሌ ፕሮፔን ፣ አይሶ-ቡቴን እና አሞኒያ የመሳሰሉትን መጠቀም አስፈላጊ በሆኑ ፖሊሲዎች ተደግፈዋል። ይህም በተመረጡ ዘርፎች ላይ ዘላቂነትና ምርታማነትን ለማጎልበት ከፈተኛ ሚና ይኖረዋል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭

ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መስፋፋት መቀጠሉን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ በበይነ መረብ መካሄዳቸውን ቀጥለዋል። የሚከተሉት ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- የዓለም አቀፍ ትዕይንት፣ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮች ክፍል፣ ግንቦት 2022 | **ምንጭ**
- የከባቢ አየር CO_2 እና CH_4 ዓለም አቀፍ ጥረት ለመደገፍ ያሉ የፋይናንስ ድጋፎች፣ የሙቀት አማቂ ጋዞችን መመዝገብ/መከታተል፣ ናሳ፣ ግንቦት 2022 | **ምንጭ**
- ለአየር ንብረት ለውጥ እርምጃዎች ማን ነው የሚከፍለው?፣ የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የስነ ሕዝብ ጉዳዮች ክፍል፣ ግንቦት 2022 | **ምንጭ**
- ዘላቂ አለም፣ ዘላቂ ጤና - በሳይንስ ላይ የተመሰረቱ መፍትሄዎች እንዴት ለውጥ ማምጣት እንደሚችሉ፣ ሰኔ 2022 | **ምንጭ**
- 2022 የአየር ንብረት ለውጥ ሳምንት፤ የአለም የአየር ንብረት ለውጥ እና ዘላቂነት ጉባኤ፣ ክላይሜት ሊንክስ፣ ነሀሴ 2022 | **ምንጭ**
- የአየር ንብረት እና የአደጋ ስጋት ፍተሻ፤ አይበገሬነትን ለመገንባት ተግዳሮቶችን መለያ ስልጠና፤ የአለም ባንክ፣ በበየነ መረብ ታግዞ ራስን በራስ የማስተማር ፕሮግራም | **ምንጭ**

ስቶክሆልም +50 – ለሀገራዊው የምክክር መድረክ ቅድመ-ዝግጅት

❑ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

ስቶክሆልም +50 በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ የተጠራና እ.አ.አ ከሰኔ 2-3 2022 በስቶኮልም ስዊዲን የሚካሄድ አለም አቀፍ ጉባኤ ነው። ይህም እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም የተካሄደውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰው ልጅ የተፈጥሮ አካባቢ ላይ ያተኮረውንና የአካባቢ ጥበቃን ለመጀመሪያ ጊዜ አንገብጋቢ የአለም ጉዳይ ያደረገውን ጉባኤ 50ኛ ዓመት ይዘክራል።

የስቶክሆልም ጉባኤ ጅማሬው መሰረት የሚያደርገው የስዊዲን መንግሰት በ1968 የአካባቢ ችግሮችን ለመመርመርና አለም-አቀፍ ትብብር የሚያስፈልጓቸውን ጉዳዮችን ለመለየት፤ የተበበበሩት መንግስታት ድርጅት አለም-አቀፍ ኮንፈረንስ ማዘጋጀት እንዳለበት የሚገልፅ ፕሮፖዛል ማስገባቱን ተከትሎ ነው። የ1972ቱ ጉባኤ ከ114 መንግስታት የተውጣጡ ተሳታፊዎች ተካፍለውበታል።

በቅርቡ የሚካሄደው ይህ አለም አቀፍ ስብሰባ የ1972ቱን የስቶኮልም ኮንፈረንስ የሚዘክር የመክፈቻ ስነስርዐትና በተጨማሪም 4 ጠቅላላ ስብሰባዎች፣ 3 የአመራር ውይይቶችንና የመዝጊያ ስነስርዐትን ያጠቃልላል።

በዚህ ስብሰባ ላይ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲሳተፉ የሚበረታቱ ሲሆን ይህም ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችንና የአካባቢ ማህበረሰቦችን እንዲሁም ሲቪል ማህበራትንና የግሉን ዘርፍ ያጠቃልላል። እነዚህ አካላት በጉባኤው ዝግጅት ወቅት እንዲሁም በጉባኤው ላይ በሚደረጉ ውይይቶች በአለም አቀፍ፣ በየቀጠናው እና በአገር አቀፍ በሚደረጉ የምክክር መድረኮች ግብዓት እንደሚሰጡ ይጠበቃል።

የሀገራዊው የምክክር መድረኩ አላማ በስቶክሆልም +50 የመወያያ አጀንዳዎች ስር ሀገርን ታሳቢ ባደረገ መልኩ፤ ሁሉን አቀፍ (መላው ማህበረሰብንና የመንግስት አካላትን) ያሳተፍ ውይይት እንዲኖር ማበረታታት ነው።

ኢትዮጵያ ለሃገራዊ ምክክር ከተመረጡት 58 ሀገራት መካከል አንዷ ናት። ይህም ሀገራዊ ምክክር በሰኔ ወር ስቶክሆልም ላይ ለሚካሄደው መድረክ በሃገራዊ እና አለማቀፋዊ ሪፖርቶች አማካኝነት ግብዓት ይሰጣል። እነዚህ ሪፖርቶች ቁልፍ ግኝቶችን፣ ምክረ-ሀሳቦችን፣ መረጃዎችን፣ የሚዲያ ሽፋኖችን እና ከሃገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፎች ጋር ያሉ ግንኙነቶችን የሚገልጹ ይሆናል።

ወደ ገፅ ፮

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ከገፅ ፭ የቀጠለ

ከዚህ ጋር በተያያዘ አለም አቀፍ ሂደቱ ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ከተደረገው የቨርቹዋል ውይይት በኋላ የተለያዩ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች በኢትዮጵያ ሲከሄዱ ቆይተዋል።

ይህም አለም አቀፍ የስብሰባው አስተባባሪዎች እ.ኤአ ከ1972 ጀምሮ በሀገሪቱ የወጡ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎች ዙሪያ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲረዳ ያዘጋጁትን መጠይቆች መሙላት እና ለብሄራዊ ምክክሩ በስዊዲን መንግስት በተመደበው 75,000 ደላር መሰረት እቅድና በጀት ማዘጋጀትና በአለም አቀፉ የመሪዎች የውይይት አጀንዳ መሰረት የውይይት ጭብጦችንና ንዑስ ርዕሶች መምረጥን ያጠቃልላል። የስብሰባውን የውይይት ጭብጥ፣ ንዑስ ርዕሶች እና አቅራቢዎችን ለመምረጥ፤ ከተባበሩት መንግስታት፣ ከመንግስት፣ ከትምህርት ተቋማት እና ከልማት አጋሮች ከተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ስብሰባዎች ተካሂደዋል። ለስቶክሆልም +50 ሀገራዊ የምክክር መድረክ የተመረጡት የውይይት ጭብጥና ንዑስ ርዕሶች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ አልበገሬነትን ለመገንባት የሚተገበሩ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ መፍትሄዎች

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የተመረጡ ንዑስ ርዕሶች፤

1. የአየር ንብረት ለውጥ ተለዋዋጭነት ሁኔታ እና በኢትዮጵያ ታዳሽ በሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ያለው ተፅዕኖ
2. የአየር ንብረት ለውጥና ተለዋዋጭነት በምግብ ስርዐት፣ አነስተኛ ግብርና፣ የአርብቶ አደር እና የአርሶ-አርብቶ አደሩ ኑሮና የምግብ ዋስትና ላይ ያለው ተፅዕኖ
3. በአየር ንብረት ተለዋዋጭነትና ለውጥ ምክንያት የሚኖረውን ተፅዕኖ ለመቀነስና አልበገሬነትን ለመገንባት መሬትን መልሶ እንዲያገግም ማድረግና የአኗኗር ዘዴን ማሻሻል ላይ የተመሰረቱ በኢትዮጲያ ያሉ ተሞክሮዎች
4. አሳታፊ መንገዶችን በመጠቀም የብዝሀ-ህይወትን መጠበቅ፣ በዘላቂነት መጠቀም፣ ፍትሀዊና በእኩልነት ጥቅምን መጋራት ዙሪያ የተስተዋሉ ስኬቶችና ተሞክሮዎች

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የአሁንና የወደፊት የአየር ንብረት ለውጥና ተለዋዋጭነት፤ በማህበረሰቡ፣ በደን፣ በጥብቅ ቦታዎች፣ ብዝሀነት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖን ያካትታሉ። ይህ የውይይት ጭብጥ በኢትዮጵያ የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትን፣ የዘለቂ መሬት አጠባበቅንና የተፋሰስ ተግባራትን ድርሻ፣ የደኖችንና የደን መሬትን ለአየር ንብረት ማስተሰረያና ማጣጣሚያ ያላቸውን ድርሻ እና የአየር ንብረት ለውጥና በዚህም ምክንያት የሚደርሰውን የሰዎች ከቦታ ቦታ ዝውውርን ያጠቃልላል።

2. የአካባቢ ብክለትና በሀገሪቱ የተወሰዱ እርምጃዎች

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የተመረጡ ንዑስ ርዕሶች፤

1. የአየርና ውሀ ብክለት በጤና ላይ ያላቸውን አደገኛ ተፅዕኖ ከመቀነስ አኳያ የተገኙ ስኬቶች
2. ከኢንዱስትሪና ከተሞች መስፋፋት ጋር በተያያዘ አደገኛ ኬሚካሎችን መጠቀምና ማስወገድ የሚያስከትለውን ጉዳት ከመቀነስ አኳያ የታዩ መሻሻሎችና የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር
3. የአከባቢ ወንጀል እና ይህንን ከመዋጋት አኳያ የኢትዮጵያ ጥረትና ያጋጠሙ ፈተናዎች
4. የፀረ-ተባይ አያያዝ እና የአደገኛ ቁሶችን ክምችቶችን ከማስወገድ አኳያ የተደረጉ ጥረቶች
5. የሀገራዊ የትግበራ ዕቅድና ለረጅም ግዜ ከአካባቢ የማይጥፉ በካዮችን (persistent organic pollutants) ከመቀነስ ወይም ከማስወገድ አኳያ በኢትዮጵያ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች
6. የኢትዮጵያ የአካባቢ ህግ የመቅረፅና የማስፈፀም ፕሮገራም
7. የፕላስቲክ ብክለት፣ የአካባቢ ችግሮችና ለአንድ ጊዜ ጠቀሜታ የሚውሉ የግብይት ቦርሳዎችን ማገድን ማስረፅ

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የሚደረጉ ውይይቶች የአየር፣ ውሃና አፈር ብክለት ሁኔታንና በሰው ጤና፣ በአካባቢና በግብርና ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ ያጠቃልላሉ። የአየርና ውሀ ብክለት የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ ከመቀነስ አኳያ የተተገበሩ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ተግባራት፣ የተገኙ ተሞክሮውችና ለወደፊት መሻሻሎች የተቀመጡ ምክረ ሀሳቦች ላይ ውይይት ይደረጋል። ውይይቱ በኢንዱስትሪዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ካሉ ኬሚካሎች ጋር እሚያያዙ ጉዳዮች፣ የደረቅ ቆሻሻዎች መጠን፣ ማዘጋጃ ቤቶች ደረቅ ቆሻሻን ከማስተዳደር አኳያ ያላቸው አቅም፣ ኬሚካሎችንና ደረቅ ቆሻሻዎችን ማስወገድን ለመቆጠጠር የሚወጡ ፖሊሲና ህጋዊ መሳሪያዎችንም ያጠቃልላል።

3. የአካባቢ ዘላቂነት በኢትዮጵያ ለመደገፍ የተነደፉ ፖሊሲዎች፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና ህጋዊ ማዕቀፎች

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የተመረጡ ንዑስ ርዕሶች፤

1. ባለብዙ ወገን የአካባቢ ስምምነቶችን በኢትዮጵያ ከመተግበር አኳያ የተነደፉ ፖሊሲዎች፣ አስተዳደራዊ መዋቅሮችና ህጋዊ ማዕቀፎች
2. የአካባቢ ዘላቂነትን ለማስፈን የተዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ስልቶች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶችን ለማስፈጽም ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ያላቸው ድርሻ

ወደ ገፅ ፮

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፫ ፣ ቁጥር ፭

ልዩ ልዩ ሀትመቶች

የአየር ንብረት ለውጥን ለማጣጣምና ለማስተሠረይ በኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ላይ የተከናወነ ዳሰሳ




የግብርናው ዘርፍ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚውም ሆነ የስራ እድል ከመፍጠር ረገድ ዋነኛው ዘርፍ እንደመሆኑ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ከመልቀቅ ረገድም የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳ። ይህ ጥናት በኢትዮጵያ በአነስተኛ ማሳዎች ላይ የተከናወኑ የማጣጣሚያ እና የማስተሠርያ ተግባራት አፈፃፀም፤ የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀትን ከመቀነስ ረገድ ያላቸውን ሚና ግምት በመውሰድ የተከናወነና የሙቀት አማቂ ጋዞችን የመቀነሻ አማራጮችን እና ተግዳሮቶችን እንዲሁም ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ አድርጓል። **ምንጭ**

የአፍሪካ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መመሪያ



ይህ ለማንኛውም አካል ተደራሽነት የሆነ መጽሐፍ በአፍሪካ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን አስመልክቶ ያለውን ወቅታዊ አስተሳሰብ ዋና ዋና ጉዳዮችን ያብራራል፤ በአህጉሩ በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችንም ይገልፃል። ከዚህም በተጨማሪ መመሪያው የአየር ንብረት ለውጥ እንዴት እንደሚጣጣም እና በአህጉሩ እንዴት በቀጣይነት ሊተገበር እንደሚችል ከተለያዩ ጥናቶችና ፕሮጀክቶች የተገኙ ልምዶችን ያስተዋውቃል። **ምንጭ**

የአየር ንብረት ለውጥ 2022፡ ተጽዕኖ፣ ማጣጣምያ መንገዶች እና ተጋላጭነት



ስድስተኛ የመንግስታት የእርስበርስ ግምገማ (IPCC) ሪፖርት የአየር ንብረት ለውጥ ተጨባጭ ለውጦችን ይገመግማል፣ ስነ-ምህዳራዊ፣ ብዝሃ ህይወትን እና ሰብአዊ ማህበረሰቦችን አስመልክቶ በዓለም አቀፍ እና በአህጉር ደረጃም ይፈትሻል። ከዚህም በተጨማሪ ሪፖርቱ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነቶችን አስመልክቶ ተፈጥሮ እና የሰው ልጆች ከአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ጋር ያላቸውን አቅም እና ወሰንም ይገመግማል። **ምንጭ**

ከገፅ ፮ የቀጠለ

3. ነባርና አዲስ እየመጡ የሚገኙን የፋይናንስ ዕድሎች ከመጠቀም አኳያ ያሉ ችሎታዎችና አቅሞች፣ ከተለያዩ ምንጮች የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ስራዎች፣ የህዝብና የግል ሽርክናን ማስፋፋት፣ በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ የካርቦን ሽያጭ ለመሳተፍ የሚያስፍለጉ ችሎታዎችና አቅሞች
4. ኮቪድ 19፤ ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ ተግባራትን በሀገሪቱ ውስጥ ከመተግበር አኳያ ያለው ተፅዕኖና አረንጓዴ የማገገሚያ መንገዶች

4. የእውቀት አስተዳደርና ኮሚዩኒኬሽን

በዚህ የውይይት ጭብጥ ስር የተመረጡ ንዑስ ርዕሶች፤

1. ፖሊሲ አውጪዎችንና ውሳኔ ሰጪዎችን ለማሳመን ዕውቀትን ማመንጨት እና ማስረጃዎቹን ማቅረብ
2. ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች ልማት፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ትምህርትና ምርምር ያላቸውን ትስስር የማጠናከርና የማሳየት አስፈላጊነት

በዚህ የመጨረሻ ጭብጥ ስር የሚደረጉ ውይይቶች መረጃን ለማመንጨት የሚረዳ የክትትልና የግምገማ ስርዐትን የማቋቋም አስፈላጊነትን፣ በተለያዩ ደረጃዎችና ተጠቃሚዎች መረጃውን ተደራሽ ማድረግን፣ ዕውቀትን ለማስተዳደር እሚያግዝ የልህቀት ማዕከል ማቋምምን፣ ተመራማሪችንና ባለሙያዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ግኝታቸውን እንዲያካፍሉ የሚረዱ ስልጠናዎችን መስጠትን ያጠቃልላል።

የሀገራዊው ምክክር የጊዜ ሰሌዳ

ይህንን ለማሳካት፤ ለሁለት ቀናት የቆዩ በአካል የሚደረጉ ሁለት ስብሰባች በሚያዝያና በግንቦት ወር 2014 በአዲስ አበባ ከተማ ይካሄዳሉ።

ስፖርክ ብሉ ባለድርሻ አካለትን እንደማሳተፊያ መድረክ ጥቅም ላይ ይውላል። ይህ የዲጂታል መድረክ ከአለም አቀፍ መድረክ ለሚሳተፉ የግልና የሲቪል ማህበራት ድምፃቸውን እንዲያሰሙ ያገለግላል። ይህም ድህረ ገፅን መሰረት ያደረገ የስፖርክ ብሉ ገፅ ለሀገራዊ ምክክሩ ጥቅም ላይ ይውላል። ሁሉም አገራት የአገራዊ ምክክሮቻቸውን አጠቃሎ የሚይዝ ድህረ ገጽ ይኖራቸዋል። ይህ ገጽም ስለ ስቶኮልም +50 ያሉ መረጃዎች፣ አገራዊ ውጤቶችና መረጃዎች፣ የአገራዊ ምክክሮቹ ዝርዝር ዘገባዎች፣ በቀጥታ የሚተላለፉ እና የተቀዱ የምክክር መድረኮች፣ ከምክክር በኋላ የተነሱ ጥያቄዎችና ውይይቶች፣ የምክክሮቹ ማጠቃለያ ጽሁፎች፣ የሚዲያ ዘገባዎችና ከ100 በላይ የቋንቋ ትርጉም ምርጫዎች ይኖሩታል።

በሚያዝያና ግንቦት ወር 2014 ላይ በአዲስ አበባ የሚካሄደው የስቶክሆልም +50 ሀገራዊ ምክክር በሀገሪቱ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችን ከመቀረፅ እና ከመተግበር አኳያ የተደረሰበትን ደረጃና ያጋጠሙ ፈተናዎች ለማሳየት ዕድል ይፈጥራል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢጥበቃ ባለስልጣን

ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150

ኢሜል: eenvironment@gmail.com;

ድረ ገፅ: https://www.epa.gov.et/

ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

ስራውን የደገፉ አካላት

Climate & Development Knowledge Network

SOUTH SOUTH NORTH
TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands

IDRC · CRDI
International Development Research Centre
Centre de recherches pour le développement international

Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.

.